"ጎሽ! ተባረክ፣ አንቺም ተባረኪ! አንትፍ አንትፍትፍትፍ ..." አሉባቸው:: "አንድምንም ብለህም ሳልሞት ብንተያይና ብመርቅህ ደስ ይለኛል" በልልኝ

# ምዕራፍ ስምንት

"የተከበራችሁ መንገደኞቻችን በካፒቴን በርይሁን እና በሥራ ባልደረቦቹ ስም ሆኜ እንኳን ደህና መጣችሁ አላለሁ:: ይህ የበረራ ቁጥር 677 ነው:: የምንበርበትም ከፍታ 35 ሺህ ጫማ ሲሆን በቀጥታ ወደ ካይሮ እናመራለን:: የምንደርሰበት ጊዜ በካይሮ ሰዓት አቆጣጠር ከሰዓት በሁዋላ 8 ሰዓት ይሆናል:: መልካም በረራ::"

ከሽንኮራ እንደመጣች ብዙም ሳትቆይ፣ ወዳጆቿን መሰነባብቱ፣ አንዱን ስትይዝ አንዱን ስትለቅ በቂ እንቅልፍ ማጣት ከጀመረች ከረምረም ስላለች አውሮፕላኑ ወደ ሚፈለግበት ከፍታ ደርሶ መምዘግዘግ ሲጀምር፣ ትርሲት ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰዳት:: ወደ ካይሮ ስትቃረብ ቀበቶዋን እንድትጣጠቅ እና ወደላይ የለጠጠችውን ወንበር እንድታቀና የበረራ አስተናጋጇ ስትቀሰቅሳት፣ አጠገቧ የተቀመጡት ሴት ወይዘሮ ውይ "ታድለሽ እኔ ምን ቢደክመኝ፣ ምን ረኸም በረራ ብበር እንቅልፍ ዝር አይልብኝም:: የሚገርም ነው፣ ጭራሽ ከጀል አያደርገኝምኮ::"

"አይ፣ እኔ የመጀመሪያየ ስለሆነ ይሆናል::"



"ኧረ! ልክ ነሽ! ሊሆን ይችላል፣ ውይ፣ የኛስ አውሮፕላን ላይ መንጠልጠል በዛ:: አንንዴማ በሳምንት 2 እና 3 አገር የምሄድበትም ጊዜ አለ::"

"ዋው! ትኬቱ አይወደድብዎትም?"

"ከመግዛትስ ገልግሎኛል፣ ባለቤቴ ኢትዮጵያ አየር ላይንስ ስለሚሠራ በሱ ነጻ ቲኬት ነው ዓለምን የምዞረው::

"በየሄዱበት አገርስ ዘመድ አለዎት?"

"አንዳንድ አገር ዘመድም ጓደኛም ይኖራል:: ግን ለአልቤርጎ የምናወጣውን ወጭ ይቀንስልናል ብለን አስው ጋ መቆየት ጉዳት አለው::"

ትርሲት ሳቅ ብላ "በነጻ መቆየት ጉዳት አለው ማለት ነው?"

"እንዴት መሰለሽ፣ አዘመድ ወይም ጓደኛ ጋ ከቆየሽ፣ ያቺንአንድ ቀን ወይም ሁለት ቀን የቆየሽባትን እንደ ትልቅ ነገር ቆጥረው ለዘመዶቻቸው እቃ ያሸክሙናል:: የነሱን እቃ ከተሸከምን ደግሞ ምኑን አተረፍነው?"

"የት ሰፈር ነው ንግድዎት?"

"ንግድ ስልሽ እኮ አየር ባየር ከጉምሩክ ሠራተኞች፣ ከትኬት ኤጀንቶች ከሆስተሶች ጋር እየተዛመድን፣ መንግሥትም ቀረጥ ክፈሉ አያለ እንዳያስቃየን የተለያዩ ዘዴ እየተጠቀምን የሩጫ የድብብቆሽ ንግድ ነው:: ብታይው አየር ባየር ንግድ እንዴት በጣም ከባድ መሰላሽ፤ እግዚአብሄር የረገመው ተረኛ የጉምሩክ ፈታሽ ካጋጠመን ደግሞ ድካማችን ሁሉ መና መቅረቱ ነው::"

የሴትየዋ ጨዋታ ለዛውን እያጣ መጥቶባት፡ አስተያየቷና የሰውነቷ እንቅስቃሴ ስለ ገረማቸው "ምነው የኔ ልጅ እንቅልፉ ተጫጫነሽ እንዴ?"

"አይ ኧረ ደህና ነኝ" አለቻቸውና አይኗን አይናቸው ላይ ተክላ "ሴባ አጭበርባሪ ነዎት፣ እንደባህል እየተቆጠረ የመጣ መጥፎ ልምድ ቀረጥ አለመክፈል እንዴት እንደጉብዝና ይቆጠራል? መንግሥት ነጋዴውን፡ ገበሬውን፡ ..በአጠቃላይ ቀረጥ መክፈል ያለባቸውን ዜጎች ካላስከፈለ እንዴት አድርጎ ዜጎቹ የሚያስፈልጋቸውን ሊያዘጋጅና ሊያቀርብ ይችላል? በእርስዎ ዓይነቱ አምታች አይነት ዜጋ ነው አገራችን ሁልጊዜ እድገቷ ወደታች የሆነው" ብትላቸው ደስታዋ ነበር::

"አይዞሽ የኔ ልጅ በይ በርታ በይ፣ አሁንማ ካይሮ እየደረስን እኮ ነው ሲሏት ነበር እይኗን ማርገብገብ የጀመረችው ውይ የኔ ነገር በወሬ ጠመድኩሽ ስምሽ ማን ይባላል? የኔ ስም ወ/ሮ አስገደች ነው ለመሆኑ መቼ ነው የምትመለሺው? ብዙ እቃ የማትይዥ ከሆነ ተቀጣጥረን አንዳንድ ዕቃ ትይዥልኝና ትንሽ አስብልሻለሁ::"

"ሆሆይ! ስሜ እንኳን ትርሲት አምባዩ ይባላል:: ኧረ እኔስ እቆያለሁ:: ስለሃሳብዎት ግን አመሰግናለሁ::"

በተነገራት መሠረት፡ ከለበሰችው ልብስ በስተቀር ያላት ተጨማሪ እቃ፣ በእጇ ያንጠለጠለችው ፎቶ ግራፍና መቀያየሪያ ያለበት አነስተኛ ሻንጣ ነው:: ወደ እንግዳ መቀበያው ስትሄድ ከውስጥ የለበሰችው አረንጓዴ፡ ቢጫ ቀይ ካኔቲራ ከላይ የደረበችውን ጃኬት ነፋስ ገለጥ ሲያደርገው በጡቶቿ ተወጥሮ



ከሩቅ ደመቅ እድርጓት ህጻን ልጅ ለማሳደግና የቤት ሰራተኛ ለመሆን ሳይሆን ኢትዮጵያን ወክላ የቁንጅና ውድድር ልትወዳደር የመጣች ነው የምትመስለው::'ፍየል ወደዚህ፡ ቅምዝምዝ ወደዚያ' ነው ነገሩ:: ሁሉም ነገር እንዳሰቡት፡ ሁሉም እንደችሎታው ቢሠማራ ምንኛ ግሩም ነበር:: እኛ የሰው ልጆች በተለይ በታዳጊ ሀገር ያለን መች ታደልና ያስብላል!

"ሄሎ ትርሲት! እንደምንድነሽ ፡ እህትሽ ፍሬ ህይወት የነገረችኝ እውነቷን ነው፣ በጣም ቆንጆ ነሽ፡ ባለቤቴም እንደምትወጅሽ ተሰፋ አለኝ:: ኢትዮጵያ እንዴት ነች? አገር ደህና ነው? ይቅርታ ስሜ ጆርጊ ነው:: በኢትዮጵያ አጠራር ደግሞ ጊዮርጊስ ነው::

" ስሜ ትርሲት ይባላል፣ አገራችንም ደህና ናት!"

"እኔ የምልሽ ምንድን ነው ነገሩ ኢትዮጵያ ችግሩ እየበዛ እየጨመረ የሚሄደው?" የአገርን ክብር የጠበቀች መስሏት "ችግርማ በሁሉም አገር አለ:: የትኛውም አገር ረሃብተኛና ሥራ-አጥ አለው::"

"ልክ ነሽ፣ ግሪክም፡ ግብጽም የሚራቡ ማደሪያ የሌላቸው ሞልተዋል:: የናንተ ግን በዛ ብዬ ነው:: እውነቱን ለመናገር እዚህ ካይሮ ውስጥ በጣም ብዙ የኢትዮጵያ ሴቶችና ወንዶች በግርድና፡ በዘበኝነት፡ የሚኖሩ አሉ:: በሌሮል የአረቦች አገር ደግሞ ከዚህም በጣም በብዙ ይበልጣሉ:: ወንዶቹ በግና ፍየል ሁሉ ይጠብቃሉ:: ሴቶች በጣም ከባድ ሥራ ለረጅም ሰዓት ይሠራሉ:: ለሴቶቹ ሥራ ካይሮ ትንሽ ቀለል ይላል:: እኔ

ትርሲት ግብጽ ውስጥ ብዙም አትቀመጥ የአቶ ጆርጊ ስራ ጸባይ በየአገሩ መዘዋወር ነው ብዙም ሳትቆይ ወደ ኤሽየ ሄዳ ፤

"ሃሎ አቶ ነቢዩ ትርሲት ነኝ፣ ሲንጋፖር ሆኜ ነው የምደውለው፣ አቢት ደውላችሁ ስታጡኝ እንዳታስቡ ብዬ ነው፡" ስትለው

"አረ አባክሽ! እንዴት ጥሩ አገር መሰለሽ!" መቼ ሄድሽ

"ታውቀዋለህ እንዴ?"

"አዎ፣ በመጠኑ አውቀዋለሁ። አንድ ሁለት ሦስት ጊዜ ሂጄበታለሁ። እንዲያውም ጊዜ ካለሽና የሚወስድሽ ሰው ካገኘሽ ሱም ሊም ታወር ውስጥ ህንጻ ቁጥር 7 የቢሮቁጥር 247 የሆነ 'ሚር አንዲ' የሚባል የህንጻው ባለቤት 'የነቢዩ ዘመድ ነኝ' በይው። እቢሮው ውስጥ ከገባሽም በግሩፕ የተነሳነውን ፎቶም ተሰቅሎ ታይዋለሽ። የፈለግሽውን ነገር ጠይቂው ይሰጥሻል። እኔምአሁን እደውልለታለሁ። ካልተመችሽ ደግሞ እሱ መጥቶ እንዲያይሽ ማድረግ እችላለሁ።

"አይ እሱ እንኳ ይቅር፣ በተለይ ወ/ሮ ኖራ ደስ አይላቸውም። አሁን እንኳን የደወልኩልህ ካረፍንበት ሆቴል እታች ወደ ፈለግህበት አገር ስልክ ማስደወያ ስላለ ነው።" ብዙ አልተቸገርኩ

"ሲንጋፖር ምን ያክል ጊዜ ትቆያላችሁ?"

"አንድ ሳምንት ነው ብለውኛል።"

"ከዚያስ ወደ ግብጽ ነው ወይስ ወደሌላ?"



"ከዚህ ዱባይ ነው ብለዋል፣ ከዚያ ወደ ግብጽ ተመልሰን የሚቀጥለው ወር ፈረንሳይ እንሄዳለን።" ይመስለኛል

"ታዲያ እንዴት ነው ያን ጉዳይ ፈረንሳይ እናድርገው እንዴ? ከፈለግሽ በጣም ቀላል ነው። ፍርየም በቀላሉ መጥታ ልታከናውነው ትችላለች። አይ ካልሽ ደሞ ትንሽ ታገሽን የተሻለ ነገር ሊያጋጥመን ይችላል።"

"ለነገሩ ይውሰዱኝ አይውሰዱኝ አላውቅም እንጂ፣ የዛሬ ሁለት ወር አቶ ጊዮርጊስ በአሜሪካን አገር ሎስ አንጀለስ የተባለ ከተማ ውስጥ የማይቀሩበት ሰብሰባ እንዳላቸው ከወ/ሮ ኖራ ጋር ሲያወሩ ሰምቻለሁ።"

"በጣም ጥሩ፣ እንዲወስዱሽ ብዙ ዘዴ መጠቀም እንችላለን። ከዘዴዎቹ አንዱና ዋነኛው ግን ህጻኑ ልጅ ብቻ ሳይሆን የተቀሩትንም ጨምሮ በጣም እንዲወዱሽ የተለያየ ዘዴ መጠቀም አለብሽ" ብሎ ሳይጨርስ "በተለይ ትንሹ ካልተኛ በስተቀር ወደ መታጠቢያ ቤት ስሄድ እንኳን ማልቀስ ጀምሯል።"

"በሱ ዙሪያ በጣም በርቺ። ምንም ሺ ጊዜ ጥሩ ሰው ብትሆንም አሜሪካን አገር ሂደሽ መቅረት እንደምትፈልጊ ለወ/ሮ ማርታም እንኳን እንዳትናገሪ!

በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ በተለይ በኢራቅ ጦርነት የተነሳ የዘይት ዋጋ መውጣትና መውረድ በሚገርም ሁኔታ ለአቶ ጊዮርጊስ አመች ሁኔታን ፈጥሮላቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊያስተላልፉት የሚችሉት ንብረት እያከማቹ ነው። ያላቸው የንብረት ብዛት እንኳንስ ምላቸውን ፓሪስ ራታቸውን

ሱንደን መብላት ቀርቶ ሲቀዱት ውሰው ቢያድሩም የሚያልቅ አይመስልም።

በቃ ሃብታም፣ በጣም ልጥጥ ሃብታም ሲኮን ሌላ ምን ይደረጋል፣ ስበብ እየፈለጉ መዞር፣ ያላዩትን አገር ማየት፣ ማስቂያ ማብቂያ የሌለውን የሰውን ልጅ ፍላጎት ለማሟላት ከባዶ እግር ጭማ፣ ባይስክል፣ መኪና ..እንዲያ እንዲያ እያለ እስከ ጀት ባለቤትነት ተደርሶም በቃኝ የለም። አንዳንዶች፣ በጣም ጥቂቶች ፈሪሃ እግዚአብሄር ያደረባቸው "አፍ ..አሁንስ በቃኝ! እስካሁን ስሥጋዩ ተሯሯጥኩ፤ እስቲ ቀሪውን እድሜየን ደግሞ ለነፍሴ ላድርግ ብለው የተራበን መመገብ፣ የተራዘን ማልበስ፣ ት/ቤት በሌለበት ማሠራት፣ ወደ መሳሰሉት ማህበራዊ ተግባራት ይሰማራሉ። ብዙዎቹ ያው እንደባዘኑ እንደተስገበገቡ ሠርተውም ሆነ አምታትተው ያጋበሱትን ንብረታቸውን ጭምድድ አድርገው ወይ ራሳቸው፣ ወይ ሌላ ሰው እንዳይጠቀምበት አድርገው የማይቀረው ሞት ይዟቸው ይሄዳል። የአንዳንዶቹማ ስማውራትም ያሳፍራል። ባንክ ቤትንም አላምን ብለው ስንት ቁም ነገር፣ ስንት ሰው ከሥራ አጥነት ሊያድን የሚችል ገንዘብ ከጉድጓድ ጉድጓድ ሲያቀያይሩ የገንዘብ ግሽበት ብራቸውን ገለባ እያደረገባቸው ስንቶቹ ከንቱ ሆነው ቀርተዋል። አንዳንዴ 'ብር እመሃይም እጅ አይግባ' የሚያስብለውም ለዚህ ነው።

አቶ ነቢዩ የሮስቶ ጊዮርጊስን ቴጀርነት ለምቶ እንደምንም ተዋውቋቸው ኢትዮጵያ ውስጥ አንዳንድ ሥራዎችን አብሮ ስመሥራት ቢዝነስ ፕላኑን አዘጋጅቶ



ሲያስረዳቸው ወጥቶ ወርዶ አመቺ ሁኔታ ሲያገኝ ባለመቻሉ ትኩረቱን ሁሉ ትርሲትን አሜሪካ እንድትሄድ ማመቻቸቱ ላይ ነው።

አባ ወልደ ሥላሴ "እየ፤ ወ/ሮ አረጋሽ፣ እኔ ከናንተ አላውቅምና፣ ልጃቸው እንደነገራችሁኝ ከግብጽ አገር ወጥታ ራቅ ብላ እስከምትሄድ ለአቶ እምባዬ ያስችበትን መንገር እያስፈልግም፤ ምክንያቱም ተነስቼ ካልሄድኩ ይላሉ። በዚያ ፋንታ 'ለጉብኝት ከጓደኞቿ ጋር ለሦስት ሳምንታት ሄዳለች፤ አቶ ገብረብሩክና ወ/ሮ አረጋሽም ተለያይተዋል፤ ዝርዝሩን ቀስ ብለው ይደርሱበታል' እንበላቸው ሲሉ "ጥሩ ነበር፣ ምነው የኛን ሰው ጸባይ እያወቁት ያገኛቸው ሰው ሁሉ እስተዛዛኝ መስሎ ከንፈሩን እየመጠጠ መደበሪያ ነው የሚያደርጋቸው። ያውም እስካሁን አለመስማታቸው በጣሙን እድለኞች ነን። እርትራ ክ/ሀገ ውስጥ እኮ ሕዝቡ እየተደበቀም ቢሆን ሌት ተቀን ነው የኢትዮጵያን የብዙሃን መገናኛ የሚሰማው። የገብረብሩክ ወንጀልም በተደጋጋሚ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ተገልጿልኮ!

የመጀመሪያ የዩኒቨርስቲ ትምህርት እንደሌሎቹ ሁሉ አንገዳግዶታል። በ30 እና በ40 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ አንብቦ ሊረዳ የሚችለውን አንዳንድ ጊዜ እስከ 2 ሰዓት ይፈጅበታል። አልፎ አልፎ የትርሲት ፎቶ በየገጹ እየተለጠፉ ማንበቡን ይጋርደዋል። ይህንንና ሌሎችንም መሰናክሎች አልፎ በሁለት እግሩ እየቆመ ስለሆነ ፊቱ በደስታ እየፈካ ነው።

አሜሪካ በጣም ጥሩ አገር ነው። እኔ በበኩሌ ጆርጊ እሽ አይለኝም እንጂ እዚያው ብኖር ደስ ይለኝ ነበር። ትርሲት! አንቺስ እንዴት ነው? ስለ አሜሪካ ምን ታስቢያለሽ?

